# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ጥቅምት 17 ቀን 2005 ዓ.ም**

**በወሎ 10 ዜጎች በፌዴራል ፖሊስ ተገደሉ፤**

**ህዝበ ሙስሊሙ የአረፋን በዓል ወያኔን በመቃወም አሳለፈ፤**

**ህወሀቶች አሁንም ኦህዴድን በአራት ከፍለው እርስ በርስ ሲያተራምሱ ሰነበቱ ተባለ፤**

**የወያኔ ቡድን ሙስሊም ባለስልጣናት ከሀገር እንዳይወጡ እገዳ መጣሉ ተጋለጠ፤**

የሙስሊሙ ህብረተሰብ በአዲስ አበባ ከተማ በወያኔ ላይ የጀመረውን ቁጣ አቀጣጥሎ በመቀጠል በተለያዩ ከተሞች ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያስተጋቡ እንደሰነበቱ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ዓርብ ጥቅምት 9 ቀን 2005 ዓ.ም በደሴ ከተማ አዋሳኝ በሆኑ ከተሞች ከፍተኛ ተቃውሞ የተስተጋባ ሲሆን ይህንኑ ተቃውሞ ለመበተን በሚል የወያኔ ቡድን በህዝበ ሙስሊሙ ላይ ከባድ አደጋ እንዳደረሰባቸው ታውቆዋል፡፡

በደቡብ ወሎ ቃሉ ወረዳ ውስጥ በተነሳ ተቃውሞ ብዙ ዜጎች በፌዴራል ፖሊስ በተተኮሰ የእሩምታ ተኩስ ወዲያውኑ ሲገደሉ ቁጥራቸው የበዙት ደግሞ ለከባድ ጉዳት እንደተዳረጉ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ህዝቡ ያልተገኘበትን ተደረገ የተባለውን የእስልምና ምክር ቤት አመራሮችን ምርጫ ተከትሎ በከሚሴ...በገርባን.....በደጋን.....በሀርቡ.....እና በሌሎችም ከተሞች በተቀሰቀሰው ተቃውሞ ላይ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዘጎች የተሳተፉበት ሲሆን ይህንኑ ተቃውሞ ለመበተን በሚል የወያኔ የፌዴራል ፖሊስ በወሰደው የእሩምታ ተኩስ ብዙ ዜጎች መገደላቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በተለይ በሀርቡ ከተማ ህዝበ ሙስሊሙ ምርጫውን ስለማናምንበት አናደርግም ብሎ አቋዋም በመውሰዱ የተደናገጡት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ጥቂት ቀስቃሽ ናቸው ብለው የገመቱዋቸውን ወጣት የእስልምና እምነት ተከታዮች አፍሰው በማሰራቸው በተቀሰቀሰ ቁጣ ከፍተኛ ተቃውሞ የተስተጋበ ከመሆኑም በተጨማሪ ህዝበ ሙስሊሙ የታሰሩትን ወጣቶች በኃይል አስፈትቶ ወደቤታቸው በመመለስ ላይ እንዳሉ የፌዴራል ፖሊስ ከሁዋላ በመድረስ የእሩምታ ተኩስ በመክፈት ወዲያውኑ አምስት ሰዎች ሲገደሉ ቁጥራቸው የበዙት ደግሞ ለከፋ ጉዳት እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

በዚሁ በፌዴራል ፖሊስ ጨካኝ እርምጃ የተበሳጨና የተናደዱ የእምነቱ ተከታይ ወጣቶች በፖሊሶቹ ላይ በወሰዱት አጸፋዊ እርምጃ ሁለቱ ወዲያውኑ ሲገደሉ ሌሎች ሶስት ደግሞ በጽኑ ቆስለው ወደ ደሴ ሆስፒታል መወሰዳቸውን በስፍራው ከነበሩ የአይን እማኞች ገለጻ ለማወቅ ተችሎዋል::

የታሰሩት የመረጥናቸው የመፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ አባሎች አሸባሪዎች ሳይሆኑ የሙስሊሙ እምነት ተቆርቋዋሪዎች በመሆናቸው በአስቸኩዋይ ይፈቱ እነሱ ሳይፈቱ ምርጫ አናካሂድም በማለት ተቃውሞ ሲያሰሙ የነበሩትን የሀርቡ ከተማ ዜጎች የወያኔ ቅጥረኛ የፌዴራል ፖሊስ ያለ አንዳች ርህራሄ በመትረየስ እና በክላሽ እሩምታ ተኩስ ዘግናኝ የሆነ ጭፍጨፋ እንደፈጸመባቸው ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በተመሳሳይ በደሴ...በከሚሴ ...በደጋን....በገርባን ከተሞች ህዝበ ሙስሊሙ ታላቅ ተቃውሞ ሲያስተጋባ የነበረ ሲሆን በተለይ በገርባን እና በደጋን ከተሞች የተደረገውን የተቃውሞ ሰልፍ ለመበተን በሚል የፌዴራል ፖሊሶች በከፈቱት ተኩስ አምስት ሰዎች የተገደሉ ሲሆን ብዙዎቹንም ማቁሰላቸው ታውቆዋል::

ከተገደሉት በተጨማሪ እነ ሐጂ መሐመድ የተባሉትን 12 ታላላቅ የእስልምና እምነት ተከታይ አባቶች አፈሰው ለእስር የዳረጉዋቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ለብርድ እና ለተለያዩ በሽታዎች በሚያጋልጡ ቆርቆሮ ቤቶች ውስጥ አስረው እያሰቃዩዋቸው እንደሚገኙ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በፌዴራል ፖሊስ እሩምታ ተኩስ ተከፍቶባቸው በጽኑ የቆሰሉ ዜጎች ወደ ደሴ ሆስፒታል የተወሰዱ ቢሆንም ህክምና እንዳያገኙ በመደረጉ በስቃይ ላይ እንደነበሩ የሆስፒታሉ ምንጮች ጠቁመው በተለይ አንድ አዛውንት ብዙ ደም እየፈሰሳቸው መሆኑን እያወቁ የህክምና እርዳታ እንዳያገኙ በመከልከሉ ህይወታቸው ሊያልፍ እንደቻለ የምንጮቹ ጥቆማ አጋልጦዋል::

የታሰሩት ይፈቱ.....በምርጫው እኛ ያቀረብናቸው እጩዎች ይሳተፉ.....ህዝበ ሙስሊሙ ሰላም ወዳድ እንጂ አሸባሪ አይደለም...አሸባሪው ህዝብን የሚያሸብር የታጠቃው ኃይል ነው....የሚሉና ሌሎችንም መፈክሮች በማንገብ በተለያዩ የወሎ ክፍለ ሀገር ከተሞች የተደረገውን ተቃውሞ ተከትሎ የተወሰደውን እርምጃ አስመልክቶ ለሆዱ ያደረው እና እምነቱን ሽጦ የሚገኘው የበረከት ስምኦን ምክትል የሆነው ሽመልስ ከማል የተሰኘው ግለሰብ ዜጎቹ መገደላቸውን አምኖ እርምጃው የተወሰደባቸው ግን ሽጉጥ.....ቆንጨራና ገጀራ ታጥቀው በመገኘታቸው ነው ሲል የማስተባበያ መግለጫ መስጠቱ ታውቆዋል::

በደሴ ከተማም ቢሆን ሙጋድ ተብሎ ከሚጠራው ሰፈር የተቀሰቀሰው ይሄው ታላቅ ተቃውሞ ሰልፍ ወደ ተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች ሊዛመት የነበረ ቢሆንም የፌዴራል ፖሊስ የተኩስ እሩምታ በመክፈት ተቃውሞውን ሊበትን እንደቻለም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የወሎ ሙስሊም ህዝብ ተቃውሞ ያስፈራው የወያኔ ቡድን እጅግ ቁጥሩ የበዛ የፌዴራል ፖሊስ ከአዲስ አበባ ወደ ስፍራው ሲያጉዋጉዝ የተመለከቱ የአይን እማኞች የተናገሩ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት አካባቢው የስጋት ቀጣና በመሆኑ የወያኔ ቡድን በጭንቀት ተወጥሮ እንደሚገኝም ተጠቁሞዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአረፋ በዓልን በስታዲየም ሊያከብር የወጣው ሙስሊሙ ህብረተሰብ በወያኔ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያስተጋባ መዋሉ ተስተዋለ፡፡እንደ ወትሮው ሁሉ ህዝበ ሙስሊሙ በዓሉን ለማክበር በስታዲየም የተገኘ ቢሆንም እስከ ዛሬ እንደሚደረገው ዝግጅቶቹን ከማከናወን ይልቅ በወያኔ ላይ ተቃውሞ ሲያስተጋባ መዋሉም ታይቶዋል፡፡

ዓርብ ጥቅምት 16 ቀን 2005 ዓ.ም ተከብሮ በዋለው በዚሁ በአረፋ በዓል ላይ ህዝበ ሙስሊሙ በአዲስ አበባ ስታዲየም በመገኘት ወያኔን የሚያወግዝ መፈክሮችን ሲያስተጋባም እንደነበር በስፍራው ከነበረው ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን የተገኘው ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የታሰሩት መሪዎቻችን በአስቸኩዋይ ይፈቱ!...የወያኔ አንብዳጆችን አንቀበልም.....ተደረገ የተባለው ምርጫ ትክክለኛ አይደለም....ምርጫው ይሰረዝ.....ሙስሊሙ አሸባሪ ሳይሆን የሰላም አርበኛ ነው.....በስማችን መነገዱ ይቁም.....በሙስሊሙ ህዝብ ላይ መቀለዱ ይቁም......የሚሉና ሌሎች መፈክሮችን ሲያስተጋቡ መዋላቸውን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ካደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በዚሁ በዓል ላይ አንድም የወያኔ ባለስልጣን ካለመገኘቱም በተጨማሪ የወያኔ አንብዳጅ የሆነው እና ከስልጣኑ ተነስቶ እንደገና የተመለሰው የእስልምና ምክር ቤት ፕሬዝዳንትም በስፍራው ሳይገኝ ህዝበ ሙስሊሙ እርስ በርስ እየተነጋገረ ተቃውሞውን እያስተጋባ ሲያወግዝ የዋለ ሲሆን የፌዴራል ፖሊስም ዙሪያውን ከብቦ ሊያስፈራራ ቢሞክርም ህዝቡ በሰላማዊ መንገድ በስታዲየሙ ውስጥ እና ውጭ ተቃውሞውን አካሂዶዋል፡፡

ከስታዲየም የተነሳው ተቃውሞ ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ ወደ ሜክሲኮ አቅጣጫ የተጉዋዘው በፌዴራል ፖሊስ ዋና መስሪያ ቤት በር ላይ ተቃውሞ ያስተጋባ ሲሆን ወደ አራት ኪሎ አቅጣጫ ያመራው ደግሞ በቤተ መንግስት በር ላይ እንዲሁም ወደ ፒያሳ እና ወደ መገናኛ የተመመው ሙስሊሙ በመንገድ ላይ ወያኔን እያወገዘ ማለፉንም ከተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የወያኔ ቡድን የሙስሊሙን ህዝብ አንገት አስደፍቶ ለመግዛት ህልምና ምኞት ቢኖረውም ህዝበ ሙስሊሙ በወሰደው ጠንካራ አቋዋም የተነሳ ክፉኛ ተቃውሞ እየደረሰበት ከመሆኑም በተጨማሪ ከግዜ ወደ ግዜ እየቀረበበት ያለው ተቃውሞ እየተስፋፋ መምጣቱን ከተለያዩ ከተሞች የሚደርሱን ጥቆማዎች ያስረዳሉ፡፡

የአረፋ በዓልን ተከትሎ በተለያዩ ከተሞች ተቃውሞ ሲስተጋባ እንደነበር የደረሰን ጥቆማ ገልጾ በተለይ በደሴና ዙሪያዋ ባሉት ከተሞች የተነሳው ተቃውሞ አስደንጋጭ በመሆኑ በፌዴራል ፖሊስ ሊበተን እንደቻለ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።

በተያያዘ ዜና አሸባሪዎች ናቸው በሚል ታፍሰው የታሰሩት የሙስሊሙ መፍትሄ አፈላላጊ የኮሚቴ አባሎች ፍርድ ቤት በያዘላቸው ቀነ ቀጠሮ ፖሊስ ሳያቀርባቸው በመቅረቱ ቤተሰቦቻቸው ሲላቀሱ እንደነበር ከአይን እማኞች የተገኘው ጥቆማ አስታወቀ።

መፍትሄ አፈላላጊ የኮሚቴ አባሎቸ እና ሌሎች የእምነቱ ተከታይ የሆኑ ጋዜጠኞችን ጨምሮ 24 እስርኞች ረቡዕ ጥቅምት 14 ቀን 2005 ዓ.ም በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቀነ ቀጠሮ ተይዞላቸው የነበረ ቢሆንም የማዕከላዊ ምርመራ ፖሊስ አዛዦች ለፍርድ ቤት ተገዥ ባለመሆናቸውና በማን አለብኝነት እስረኞቹን ሳያቀርቡ መቅረታቸው ታውቆዋል።

በተያዘላቸው ቀን እና ሰዓት ፍርድ ቤት ይቀርባሉ ተብሎ ወዳጅ ዘመዶቻቸውና የሙስሊሙ እምነት ተከታይ የሆኑ ደጋፊዎቻቸው ከጠዋቱ 3 ሰዓት ጀምሮ እስከ 11 ሰዓት ተኩል ድረስ ቢጠብቁም እስረኞቹ ሳይቀርቡ በመቅረታቸው ቤተሰቦቻቸው በጭንቀት ተውጠው ሲላቀሱ እንደነበር ታውቆዋል።

ሙስሊሙ ህብረተሰብ ወያኔ ያስቀመጣቸው የእምነቱ ተከታይ ካድሬዎች አይመሩንም ብሎ አቋዋም ከመያዙ ጋር ተያይዞ መፍትሄ አፈላላጊ ይሆናሉ ተብሎ የተመረጡት እነኚሁ የኮሚቴ አባሎች ለወያኔ እንደማይወግኑና ከወያኔ ጋር አብረው እንደማይሰሩ በመግለጻቸው የተነሳ አሸባሪዎች ናቸው በሚል የሀሰት ታፔላ ለጥፎባቸው ለእስር የዳረጋቸው ሲሆን ከተያዙበት ቀናት ቆይታ በሁዋላ ለይስሙላም ቢሆን ፍርድ ቤት እያቀረቡ ጊዜ ቀጠሮ እየተሰጣቸው የነበረ ቢሆንም ረቡዕ ዕለት ግን አለመቅረባቸው ያሳሰባቸው በመሆኑ ቤተሰቦቻቸው በፍርድ ቤት ግቢ ውስጥ ሲላቀሱ እንደነብ ተስተውሎዋል።

እራሱ ያወጣውን ህግ እራሱ እየጣሰ ያለው የወያኔው ቡድን ሙስሊሙን አንበርክኮ ለመግዛት ካለው ህልም የተነሳ እኔ ያልኩትንና እኔ የማስቀምጣቸውን ሰዎች አሜን ብላችሁ ተቀበሉ በሚል በታጣቂ ኃይል ጭምር እርምጃ እየወሰደ ቢሆንም ሙስሊሙ እስከ ህይወት መስዋዕትነት እየከፈለ ባለበት በዚህ ግዜ አስተባባሪ ናቸው ተብለው በሙስሊሙ የተመረጡትን ዜጎች አፍሶ አሸባሪ ናቸው በሚል ለእስር ከመዳረጉም በላይ ፍርድ ቤት ሳያቀርባቸው በመቅረቱ በሙስሊሙ ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ ሊቀሰቀስ እንደሚችል ከወዲሁ እየተፈራ መሆኑ ተጠቁሞዋል።

ከነሐሴ ወር አጋማሽ ጀምሮ ለእስር የተዳረገችው የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣኑና በቅርቡ ከኦህዴድ ስራ አስፈጻሚነቱ የተወገደው ጁኔዲ ሳዶ ባለቤትም ከ24ቱ እስረኞች ጋር አንድ ላይ የምትገኝ መሆንዋንም ለቤተሰቦችዋ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልጸዋል።

ከሳዑዲ ኤምባሲ 50 ሺህ ብር እና 500 መጻህፍትን ይዛ ስትወጣ ከበር ላይ ተይዛ ለእስር በተዳረገችበት ወቅት ጁኔዲ ሳዶ ባለቤቱን አስመልክቶ በበተነው የድረሱልኝ ጥሪን ተከትሎ በደህንነት ሲዋከብ ከመሰንበቱም በተጨማሪ ባለፈው አስራ አምስት ቀን የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አዳማ ላይ

ባደረገው ስብሰባ ከስራ አስፈጻሚነቱ ያሰናበተው ከመሆኑም በተጨማሪ ከሀገር እንዳይወጣ መከልከሉንም ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቁመዋል፡፡

ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ አስቀድሞ በተያዘ ፕሮግራም መሰረት ወደ አሜሪካ ሚኒሶታ ግዛት የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችን ለማነጋገር ወደ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ከተጉዋዙት ልዑካን መሀከል ከሀገር መውጣት እንደማይችል ተነግሮት የተመለሰው ጁኔዲ ሳዶ በቁም እስር ላይ ሆኖ የመጨረሻውን ውሳኔ እንዲጠባበቅ እንደተነገረውም እነዚሁ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጠቁመዋል፡፡

በቅርቡ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው የእስልምና እምነት ተከታዩ ደመቀ መኮንን ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳለው የተነገረለት ጁኔዲ ሳዶ ወደ አሜሪካ እንዲሄድ ፍቃድ የሰጠው መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ ሌሎች የህወሀት ባለስልጣናት ሳያውቁት ፍቃድ ማግኘቱን ተከትሎ በደመቀ መኮንን ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ መከሰቱንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በወያኔ ቡድን ውስጥ ስር የሰደደ ችግር እየተገላበጠ ባለበት በዚህ ወቅት ሙስሊሙ ህብረተሰብ እያነሳ ያለውን ጥያቄ ተከትሎ በእስልምና እምነት ተከታይ ባለስልጣናት ላይ ደህንነቶች ልዩ ክትትል እየተደረገባቸው ከመሆኑም በላይ ብዙዎቹ ከሀገር እንዳይወጡ እየታገዱ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

በወያኔ ቡድን ውስጥ የተዳፈነው እሳት ድንገት እየተነሳ እርስ በርስ ሲያናክሳቸው የሰነበተ ሲሆን በተለይ የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት እስከ መቼ ስልጣን ተነፍገን እንቆያለን...በሚል አኩርፈው የነበረ ቢሆንም የሁዋላ ሁዋላ ላይ ግን እነ በረከት ኦህዴድን በአራት ከፍለው ሲያተራምሱት መክረማቸው ታውቆዋል፡፡

የመለስን መሞት ተከትሎ የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት የተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የሆነውን አባዱላ ገመዳን ወደ ክልሉ ፕሬዝዳንትነት ለመመለስ እና አለማየሁ አቶምሳን ለማባረር ሲያደርጉት የነበረውን ሙከራ የህወሀቱ ቡድን እንዳመከነውም ተጠቁሞዋል፡፡

ኦህዴድን አሁንም ድረስ የኦነግ ተቀጽላ ብለው የሚፈርጁት የህወሀት ሰዎች አባዱላ ገመዳን ከፌዴራል ስልጣኑ አንስቶ ወደ ክልሉ ለመውሰድ የነበረውን የኦህዴድ ባለስልጣናት ዘመቻ ቡድንተኛ በሚል ከመርጃቸውም በተጨማሪ አስቸኩዋይ ግምገማ ተደርጎ ውስጥ ውስጡን የሚያደራጁ ናቸው የተባሉትን ከኃላፊነታቸው አንስተው ውጤቱ እንዲገለጽላቸው ትዕዛዝ ቢሰጡም የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ግን እንዳችም የማባረር እርምጃ ሳይወስድ በመቅረቱ የተነሳ ከፍተኛ ቅሬታ በወያኔ ቡድን ውስጥ መፈጠሩን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ያስረዳል፡፡

ኦህዴድን በአራት ከፍለው እርስ በርስ ሲያተራምሱ የሰነበቱት የህወሀት ሰዎች እና እነበረከት ኦህዴድ መለስ .....ኦህዴድ አባዱላ.....ኦህዴድ ኦሮሚያ እና ኦህዴድ አድፋጭ በሚል ሲያተራምሱዋቸው እንደነበርም የስብሰባውን ሂደት የተከለታተሉ ወገኖች አጋልጠዋል፡፡

ኦህዴድ መለስ የተባለው ቡድን የመለስን ራዕይ እናሳካለን ብሎ የሚያምን ሲሆን...... ኦህዴድ አባዱላ የተባለው ቡድን ደግሞ አባዱላ ወደ ክልሉ ይመለስ የሚሉ ሲሆን...... ኦህዴድ ኦሮሚያ የተሰኘ

ው ቡድን አራማጆች ደግሞ ኦሮሚያን በሁሉም መንገድ ማጠናከር ብሎ የሚያምን እንደሆነና ኦህዴድ አድፋጭ የተባለው ደግሞ ከየትኛውም ቡድን ያልወገነ ግን ስልጣን ከሚይዘው ጋር ሊለጠፍ የተዘጋጀ መሆኑን ስብሰባውን የተከታተሉ ወገኖች በዝርዝር አስረድተዋል፡፡

ኦሮሚያን ለመቆጣጠር ህወሀት ከነበረው የቆየ ህልም ገና በረሀ እያሉ ሙሉጌታ አለምሰገድ (ጫልቱ) እና ክንፈ ገብረ መድህንን የተባሉትን እያሰረገ በማስገባት በተለያዩ ቦታዎች የስለላ ስራ ሲያሰራቸው የቆየ ሲሆን ህወሀት ወደ ስልጣን ከመጣ በሁዋላም ከኦህዴድ ጀርባ በመሆን ኦሮሚያን ሲያምሱ የነበረ ቢሆንም አሁን መለስ ከሞተ ወዲህም ተደናግጠው ኦህዴድን እያመሱት ይገኛሉ ሲሉም የዚሁ ድርጅት አባሎች በቁጭት ይናገራሉ፡፡

እነዚሁ የድርጅቱ አባሎች አክለውም ህወሀቶች በሁሉም መስፈርት አናሳ በመሆናቸው ኦህዴድ ወደ ስልጣን ከወጣ ጨርሶ ያጠፋናል የሚል ግምት እና ስጋት ስላላቸው ድርጅቱ እንዳይፈርስ ደገፍ እያደርጉ..... እንዳይጠናከር ደግሞ እየኮረኮሙና እርስ በርስ እያናከሱ የሚገኙ በመሆኑ አሁንም የሰሞኑ ትርኢት የዚሁ አካል አንዱ ገጽታ ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

ከሻዕቢያ በውሰት የመጡት እና ምርኮኛ በሆኑት በእነ ኩማ ደመቅሳ ...አባዱላ ገመዳና ሌሎች ጀርባ እየተጠቀሙ ያሉት ህወሀቶች በተለይ መለስ ከሞተ በሁዋላ ቀኑ ጨልሞባቸው .....የሚያደርጉት ጠፍቶዋቸው .....ቀን ከሌት ሲመክሩና ሲዘክሩ ከርመው አዲስ የመበታተኛ ስልት አዘጋጅተው እርስ በርስ ሲያወዛግቡዋቸው ቢከርሙም እንዳሰቡት ሳይሆንላቸው መቅረቱም ሌላው የህወሀት ራስ ምታት ነው ሲሉም ይገልጻሉ፡፡

በአሁኑ ሰዓት በወያኔ ቡድን ውስጥ የማይጠፉ እሳት ተዳፍኖ የሚገኝ መሆኑን የጠቆሙት እነዚሁ የድርጅቱ አባሎች ህወሀቶች አሁንም የበላይ ለመሆን የሚያደርጉትን ሩጫ ለመግታት ከሌሎቹ በተለይ ኦህዴድ ውስጥ ውስጡን እየሰራ ነው ሲሉም ይገልጻሉ፡፡

በመጨረሻም ወያኔ በፈጠረው የጎሳ ፖለቲካ ምክንያት በደቡብ ክልል ውስጥ በተከሰተ ግጭት ለብዙ ቀናት መንገዶች ተዘጋግተው እንደሰነበተ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገለጸ፡፡

ግልገል ግቤ ቁጥር 3 የኃይል ማመንጫ በሚገነባበት በኦሞ ዞን አካባቢ ባለፈው ወር የተጀመረው የእርስ በርስ ግጭት የተነሳ የኤሌክትሪክ ግድብ ስራው ለ15 ቀናት ተቋርጦ እንደሰነበተም ይሄው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በአካባቢው በተከሰተ ችግር የተነሳ እርስ በርስ በሚያደርጉት የተኩስ ልውውጥ ምክንያት ከዚህ ቀደም ወደ ቦታው ይገቡ የነበሩ ቱሪስቶች ሙሉ ለሙሉ ያቆሙ ከመሆኑም በተጨማሪ ለግድቡ ስራ የሚገቡና የሚወጡት ሰራተኞች በስፍራው እንዳይንቀሳቀሱ በመከልከላቸው ለብዙ ቀናት ስራ ቆሞ እንደነበርም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

የወያኔ ቡድን የፌዴራል ፖሊሶችን ወደ ስፍራው ልኮ የነበረ ቢሆንም የአካባቢው ነዋሪዎች በተኩስ መልሰው ያባረሩዋቸው መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡